ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
efdpu@aol.com www. Finote.org

ፕሮግራም፡ ረቡዕና እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰዓት እስከ ሶስት ሰዓት በ 25 ሜትር ባንድ
**Program**: Wednesday and Sunday 8:00PM- 9:00 PM on 25 meter band

# ዜና ዘገባ

ህዳር 18 ቀን 2003 ዓ. ም.

**የባህልና የቱሪዝም ሚኒስቴር ሠራተኞች ከስራ ተባረሩ**

**በጎረቤት አገሮች የሚኖሩ ስደተኞች ኢትዮጵያውያን ከፍተኛ ችግር እያጋጠማቸው ነው፣**

**በግድ እየታፈሱ ወደአገራቸው እንዲመለሱ እየተደረጉ ነው**

**የቴሌኮሙኒኬሽን ድርጅት አስተዳደር ስራ የፈረንሳይ ቴሌኮም ሊረከበው ነው**

**በሱዳን የእርስ በርስ ግጭት ሊነሳ ይችላል ተብሎ ስጋት አሳድሯል**

**ወያኔና ግብጽ መወነጃጀል ጀመሩ፣ የወያኔ ቡድን ጦሩን በተጠንቀቅ እንዲቆም አዘዘ**

---

የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር ሠራተኞች በመሥሪያ ቤቱ ውስጥ የተከሰቱ ሙስናዎችን በማጋለጣችን ከኅዳር 1 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ ከሥራ ታገድን በማለት ኣማረዋል፡፡ ሠራተኞቹ ከሥራ ሊታገዱ የቻሉት ‹‹ብዝኀነትን ለዘላቂ ልማትና ለማኅበራዊ ለውጥ መጠቀም›› ለተሰኘ ፕሮጀክት ማከናወኛ በማለት የስፔን መንግሥት የሰጠውን የአምስት ሚሊዮን ዶላር ዕርዳታ ያለ አግባብ ሲባክን በማየታቸው ወያኔ ፍትሕ ሚኒስቴርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ለሚላቸው መረጃ በመስጠታቸው እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ይህ የሙስና ውዝግብ የአፋርን ሕዝብ ትግል አሳልፎ ስጥቶ በወያኔ የተሾመውን የቀድሞውን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ መሓሙዳ አህመድ ጋአስንም ይመለከታል ተብሏል። ፍትሕ ሚኒስቴር

ድርጅቶቹ በቅድሚያ ክፍያ መልክ የወሰዱትን ገንዘብ እንዲመልሱ ለማለት የቻለው የባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር በቁጥር 1/9-7/167 ሰኔ 22 ቀን 2002 ዓ.ም. በተጻፈ ደብዳቤ ባሳሰበው መሠረት መሆኑ ተገልጿል፡፡ ጨረታውን በማሸነፍ ደረጃም ሆነ ለፕሮጀክቱ አማካሪ በመሆን ረገድ አስራሩ ህገወጥ ሙስናን ማንጸባረቁም ሊታወቅ ተችሏል።

አግባብ ያልሆኑ ሥራዎችን ከስሩት ከስምንቱ ድርጅቶች ውስጥም ሲ.ኤች.ሲ የተባለው ድርጅት ብቻ የወሰደውን የ300 ሺሕ ብር ቅድሚያ ክፍያ የመለሰ ሲሆን ቀሪዎቹ ሰባቱ ግን ለመመለስ ፈቃደኛ አለመሆናቸውን ገልጸዋል። ጉዳዩን ይዘውት የነበሩት ሠራተኞች መታገዳቸው ሙሰኞችን ለማጋለጥና ለመክሰስ የተጀመረውን ሥራ የሚያደናቅፍና የማጣራቱ ሒደት እንዲቋረጥ የሚያደርግ ነው ተብሏል፡፡ በወያኔ የተመሰረተው ጸረ ሙስና ኮሚሽን ዋና ስራው ከመለስ አገዛዝ ያልተስማሙትን መክሰስና ማጋለጥ እንጂ ሌላ ባለመሆኑ ዋናዎቹ የሙስና ተጠያቂዎች ማለትም መለስና ባለቤቱ፤ ዘመዶቹና የወያኔ ባለስልጣናት የሚፈሩት ክስ ከቶም የለም ተብሏል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብርሀብና ችግር እየተጠበሰ ባለበት በአሁኑ ጊዘ ራሱን ብአዴን ብሎ የሚጠራውና የወያኔ ተለጣፊ የሆነው ቡድን የተመሰረትኩበትን 30ኛ ዓመት አከብራለሁ በሚል ብዙ መቶ ሚሊዮን የሕዝብ ብር እያጠፋ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ሕዝብን በግድ አዋጣ ብለው ከወሰዱት ገንዝብ ውስጥም በ 19 ሚሊዮን ብር የቡድኑ መስሪያ ቤት ህንጻን አሰርተዋል። ከዚህ በላይ ገንዘብም ባክኖ ለወያኔ አድረው ሀገራቸውን ለጎዱ ስማዕት ተብዬዎችም ሀውልት ቆሞላቸዋል። በአሁኑ ጊዜ ብአዴን ተብዬው ቡድንን የሚያዙትና የሚመሩት እንደ በረከት ዓይነቶቹ ኤርትራውያን መሆናቸውም የአደባባይ ምስጢር ነው። ቡድኑ ነፍስ የሌለው የወያኔ ተለጣፊና በአማራው ሕዝብ ላይ የተጫነ መቅሰፍት መሆኑንም ሕዝብ ሁሉ ያውቃል። የምስረታው በዓልነት ለወያኔ በመሆኑ ሕዝብን የሚመለከት አይደለምም ተብሏል። የብአዴን መሪዎች ኢትዮጵያ ነጻ ስትወጣ ከነመለስ ጋር ሆነው ለፈጸሙት ወንጀል ሁሉ ተጠያቂ መሆናቸው አያጠራጥርም ተብሏል።

በተያያዘ ዜና የመለስ ቡድን ኢ.ሕአፓን ለማጥፋት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አጠናክሮ በጀመረው ዘመቻ የዚሁ የብአዴን መሪዎች ልዩ ግዳጅ እንደተሰጣቸው ለማወቅም ተችሏል። ህላዌ ዮሴፍ፤ በረከት ስምኦን፤ አዲሱ ለገሰና ሌሎችም ቀድሞ ያውቋቸው የነበሩ የኢ.ሕአፓ አባላትን እየተገናኙና ከውጭ ሀገራትም እየጋበዙ፣ ከዚህ በፊት በፎረም 84 ሞክረው የከሸፈባቸውን ነፍስ ሊዘሩበት እየጣሩ መሆናቸው ተደርሶብታል። አስቴር ማሞ የተባለችው የወያኔ ሎሌም በአሜሪካ በመዟዟር ወጣቶችን ማደራጀት በሚል እየሞከረች ያለችውም ከዚሁ የተያያዘ ነው ተብሏል። ከአሜሪካና ከአውሮጳ ወደ አዲስ አበባ እየተጓዙና ቤትና ንብረት እያስመለሱና ከተለጣፊዎቹ እየተገናኙ የሚመለሱትን እናውቃቸዋለን፤ እየተከታተልናቸውም ነው ብሎ ኢ.ሕአፖ አሳውቋል የሚሉ ክፍሎች በቅርቡ የመለስ የጸጥታ ጉዳዮች አማካሪ ጸጋዬ በርሄ፤ በጸጥታ መስሪያ ቤት ዋና ሀላፊዎች ኢሳያስና ጌታቸው፣ እና በጸጥታው መስሪያ ቤት የኢ.ሕአፓ መምሪያ ሀላፊ ምስጢር ስብሰባ ማድረጋችውም ተጋልጧል። ኢ.ሕአፓ ባለፈው

ወር በአዲስ አበባ ከተማ አርማውን ያዘሉና ጸረ ወያኔ ትግላችን ይፋፋም የሚሉ መልዕክቶችን የያዙ ወረቀቶች በመለጠፉና በማሰራጨቱ የወያኔ ጎራ መደናገጡ የሚታወቅ ነው። ድርጅቱንም ለመከፋፍልና ለማዳከም ወያኔ ብዙ ጥሮ ያልተሳካለት መሆኑን ማመን ስለተገደደ ዛሬ እነሆ በአዲስ ከሀዲዎችና ተለጣፊዎችን አጠናክሮ ሊያሰማራ ተነስቷል። ወያኔ በውጭ ሀገር ያሉ ዜጎችን ለመከፋፈል መድቦ የነበረው ገንዘብ ላይ ጭማሪ ማድረጉም ታውቋል። አንዳንድ ከሃዲዎች በአሜሪካና አውሮጳ የሚያደርጉትን ጉዞ ወጪ ሽፋኝም ወያኔ መሆኑ ግልጽ ነው። የሕዝብ ወገን መስለውና ተመሳስለው ድርጅቶችን ሊከፋፍሉና ሊጎዱ የተቀጠሩትን በተመለከተ ዜጎች ሁሉ ነቃ ብለው መገኘት አለባቸው ተብሏል።

በርካታ የኢትዮጵያ ስደተኞች ለሞት መዳረጋችው ያነሰ ይመስል፣ ብዙዎች ደግሞ ወደ ወያኔ በግድ እየተመለሱ ናቸው - ከሱዳን፤ ከኬንያ፤ ከጅቡቲ፤ ከየመን አልፎም ከአውሮጳ ሀገሮችም። ባለፈው ሰሞን ጅቡቲ ብዙ ስደተኞችን አፍሳ ለወያኔ አስረክባለች። የኬንያ መንግስት ከሻዕቢያ ጉቦ ተቀብሎ በመሬቱ ኦነግ ጦር ሰፈር እንዲከፍት የፈቀደ ሲሆን ከወደ ወያኔ ደግሞ ክፍያው በዛ ሲል እነዚሁኑ ማጋፈጡንም የተለመደ ነው። በዚህም መሰረት ካለፉት ሳምንታት ጀምሮ የኬንያ ጦር በወያኔ ታግዞ በድንበር አሉ በሚላቸው የኦነግ ታጣቂዎች ላይ ጥቃት ፈጽሜ ድልን ተቀዳጀሁ ብሎ ለፍፏል። ያዝኳቸው ያለውን እስረኞችንም ለወያኔ ሊያስረክብ መወስኑንም ገልጿል። ማንም የአካባቢውን ሁኔታ የሚያውቅ ሊገምት እንደሚችለው የኬንያ መንግሥት ስደተኞችን ለወያኔ ሊያስረክብ መወስኑ አገርሽቶበታል ማለት ነው። የመለስን ቡድን መደገፍ አለባችሁ የሚለው ዕዝ ከወደ አሜሪካን እንግሊዝ መተላለፉ ደግሞ ምስጢር አይደለም። ስደተኛን የሚያጎሳቅሉና የሚያባርሩን የጎረቤት ሀገሮች በተመለከተ የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ በተደጋጋሚ እንዳቀረበው የማያቋርጥ ተቃውሞና ማጋለጥ መካሄድ አለበትም ተብሏል።

የቅድስት ሥላሴ መንፈሳዊ ኮሌጅ ከህዳር 8 ቀን 2003 ዓ.ም. ጀምሮ የምግብና የትምህርት አድማ የመቱ ከመቶ በላይ የሆኑ ተማሪዎችን (ደቀመዛሙርት) ወደ ትምህርት ገበታቸው የማይመለሱና የኮሌጁን ምግብ የማይመገቡ ከሆነ፣ የኮሌጁን ንብረት አስረክበው የትምህርት ተቋሙን በአስቸኳይ ለቀው እንዲወጡ ከትናንት በስቲያ አስታወቀ፡፡ ተማሪዎቹ ማለትም መነኮሳት፣ ቀሳውስት፣ ዲያቆናት፣ መሪ ጌታዎችና ሌሎችም አድማውን የመቱበትን ምክንያት ሲያስረዱ፣ ‹‹የምንመገበው ምግብ በባእድ አምልኮ የተመረዘ በመሆኑ ለተለያዩ በሽታዎች እየተጋለጥን ነው፡፡ ለዚህም ደግሞ ኃላፊነቱን የሚወስዱት የምግብ ቤቱ ኃላፊ በመሆናቸው ከሥራቸው ይባረሩልን፤›› ነው የሚሉት፡፡ የተማሪዎቹ የተቃውሞ መነሻ የሆነው የምግብ መመረዝና የባእድ አምልኮ ግንኙነት ምን እንደሆነ አልተብራራም፡፡ ይህ ይባል እንጂ የተቃውሞ መሰረቱ የወያኔውን ጳጳስ ተብዬ አባ ገብረመድህንን በመቃወም መሆኑም ይነገራል። ኮሌጁም በአባ ገብረመድህን ሹመኞችና የክልል አንድ ተወላጆች መያዙም አነጋጋሪ ከሆነ ውሎ ያደረ ጉዳይ መሆኑም ተጥቅሷል። የኮሌጁ አንድ ሀላፊ መምህር ፍስሓ ጽዮን ከተማሪዎቹ ጀርባ በመሆን እያበረታታና ገንዘብ እየሰጠ አድማው እንዲቀጥል የሚያደርግ አካል ይኖራል ሲሉ ከሰዋል፡፡ ትምህርታቸውን በተመለከተ

ተማሪዎች ያቀረቡትንም ሀሳብ መምህሩ ውድቅ አድርገዋል።

የቴሌኮሙኒኬሽን ድርጅት ብልሽትሽት ያለ መሆን ገሀድ ቢሆንም ለሁለት ዓመት አስተዳዳሪ ተብሎ የፈረንሳይ ቴሌኮም መሰየሙ አነጋጋሪ ሆኗል። የፈረንሳይ ፕሬዚዳንት ሳርኮዚ በመጪው ጥር አዲስ ኣበባን ይጎበኛል የተባለው ወያኔ ለፈረንሳይ ኩባንያዎች አመቺ ሁኔታ እየፈጠረ በመሆኑ ነው የሚሉም ኣሉ። ፍራንስ ቴለኮም ኩባንያ ራሱ በአብላጫው የፈረንሳይ መንግስት ንብረት መሆኑ ሲታወቅ በአስራሩ ራሱ ችግር እንዳለበት የሚታወቅ ነው። በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ቴሌ ከወያኔ እጅ መውጣቱ ደግ ነው የሚሉ ጥቂቶች ባይሆኑም የቴሌ ችግር የአስተዳደር ሳይሆን የወያኔ ቁጥጥር ነው ተብሏል። ወያኔው የቴሌ ሀላፊ ደብርጽዮን/ ለምሳሌ የስለላና ቁጥጥር ስራ እንጂ ሌላ ተልዕኮ አልነበረውም። የፈሬንሳይ ኩባንያዎች ለታምራት ላይኔ ጉቦ ሰጡ ተብለው ቀደም ሲል የተከሰሡ መሆናችው ሲታወስ ኣሁንም እንደ ቻይናና ጣሊያን ኩባንያዎች ጉቦ በመስጠት ጨረታ አሸናፊ እንደሚሆኑ ታውቋል። ወያኔ የኢንተርኔት ግንኙነቶችን መቆጣጠር መፈለጉና መቆጣጠሩም የሚታወቅ ነው። ወያኔ በተጨማሪ ስልኮችን ይጠልፋል፣ ድረገጾችን ያግዳል--እግረ መንገዱንም ቴሌውን ያበላሻል። የመለስ ሚስት አዜብ በግሏ ሳተላይት ዲሾችን አስገብታ ቴሌን ብዙ ሚሊዮን ብር ማክስሯ ሲታወቅ፣ እሷም ሆነች ተባባሪዎቿ እንዳይከሰሡ ደግሞ መለስ መከልከሉን አዋቂዎች ይናገራሉ።

ህዳር 14 ቀን 2003 ዓ.ም በአዲስ አበባ በተደረገው የምስራቅ አፍሪካ ሀገራት (ኢጋድ) መሪዎች ስብሰባ ላይ የተገኘውና በሱዳን የእርስ በርስ ውዝግብ መፍትሔ ይሰጣል ተብሎ ሲጠበቅ የነበረው መለስ ዜናዊ ባሰበው መንገድ ሁለቱ ወገኖች ስምምነት ላይ ባለመድረሳቸው በመበሳጨት ስብሰባውን አቋርጦ ከመውጣቱም ሌላ ወዳጄ የሚለውን አልበሽርን ሳይሸኘው እንደቀረም ታውቆዋል::

ጥር 1 ቀን 2003 ዓ.ም በሰሜን ሱዳን እና በደቡብ ሱዳን ህዝቦች በኩል አንድነት ወይም ልዩነት በሚል የመጨረሻ ህዝበ ውሳኔ ይደረግበታል ተብሎ እየተጠበቀ ባለበት በአሁኑ ወቅት ሁለቱ ቡድኖች በአቤይ ግዛት ላይ ስምምነት ይደርሳሉ ተብሎ ከፍተኛ ተስፋ ተጥሎበት የነበረ ቢሆንም የተባለውና የተገመተው ሳይሆን በመቅረቱ በአካባቢው ከፍተኛ ውጥረት መንገሱም ታውቆዋል::

የምስራቅ አፍሪካ መሪዎች ስብሰባ ከጥቅምት 20 ቀን 2003 ዓ.ም ጀምሮ ለተከታታይ ቀናት በኬንያ ናይሮቢ ሊደረግ የነበረ ቢሆንም በሱዳኑ ፕሬዝዳንት አልበሽር ላይ የዓለም አቀፉ የወንጀለኞች ፍርድ ቤት የእስር ማዘዣ በማውጣቱና ኬንያም የዚህ ድርጅት አባል በመሆንዋ እንድታስረክብ ስለምትገደድ ከአጣብቂኙ ለመውጣት ስትል ስብሰባው ወደ ኢትዮጵያ ተዛውሮ እንዲደረግ ባቀረበችው መሰረት ጉባዔው በአዲስአበባ እንዲካሄድ የተደረገ መሆኑ ይታወሳል::

የኢጋድ የመሪዎች ስብሰባ ከመደረጉ አንድ ሳምንት አስቀድሞ የደቡብ ሱዳን አማፂ ቡድን አንድ ልዑክ በምስጢር አዲስ አበባ መጥቶ ከመለስ ዜናዊ ጋር ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ ምሽቱ 4 ሰዓት ድረስ በቤተ መንግስት ውስጥ ውይይት አድርገው እንደነበር የተጠቆመ ሲሆን ከዚህ ውይይት እና ምክክር አንዳችም ፋይዳ ባለማግኘቱ

ያሰበው የግል ዝና በመቅረቱ ሳይሸኛቸው በተቀመጡበት ጥሎዋቸው እንደሔ ደም ተነግሮዋል፡፡

የጉባዔውን መጠናቀቅ ተከትሎ የወያኔው መሪ መለስ ዜናዊና የኬንያው መሪ ሙዋይ ኪባኪ በጋራ አጠቃላይ መግለጫ ይሰጣሉ ተብሎ ሲጠበቅ የነበረ ቢሆንም መለስ አኩርፎ አስቀድሞ ከስብሰባው ወጥቶ በመሄዱ የተነሳ መግለጫ ሳይሰጡ በመቅረታቸው የሱማሊያ ፕሬዝዳንት ተወካይ መግለጫውን ለመስጠት እንደተገደደ ለመረዳት ተችሎዋል፡፡

ከ200 ሺህ ህዝብ በላይ የጨረሰውና ቤት ንብረት ላወደመው የሁለቱ ቡድን ግጭት ዘላቂ መፍትሔ ይሆናል ተብሎ ብዙ ውጣ ውረዶች በዓለም አቀፍ ለጋሽ ድርጅቶችና በተባበሩት መንግስታት ድርጅት ጭምር ሙከራ ሲደረግ ቆይቶ የነበረ ቢሆንም ህዝበ ውሳኔ ሊደረግ የአንድ ወር ግዜ በቀረው በአሁኑ ሰዓት ሁለቱም ወገኖች በያዙት ግትር አቋዋም ምክንያት ሳይስማሙ በመቅረታቸው በአካባቢው ችግር ሊፈጠር ይችላል ተብሎ ከፍተኛ ስጋት አሳድሮዋል፡፡

በደቡብ ሱዳን ይዞታ ስር የሚገኘው ከፍተኛ የነዳጅ ክምችት ያለው የአቤይ ግዛት ዕጣ ፈንታ ምን ይሁን በሚለው ጉዳይ ላይ የሱዳን መንግስት እና የደቡብ ሱዳን መንግስት ሲወዛገቡና ሲደራረደሩ የነበረ ሲሆን ባለፈው ወር መጨረሻ ላይም በአሜሪካ መንግስት አደራዳሪነት ሰላም ለማውረድ አዲስ አበባ ውስጥ ጥረት አድርጎ የነበረ ቢሆንም ይሄም ሳይሳካ ቀርቶዋል፡፡

ሁለቱ ቡድኖች ከዕለት ወደ ዕለት ልዩነታቸውን እያሰፉ ባለበት በዚህ ወቅት አልበሽር ከራሺያ ከባድ የጦር መሳሪያን ጨምሮ ከ10 በላይ ተዋጊ የጦር ሄሊ ኮፕተሮች ገዝቶ እንዳስገባና አማፂ ቡድኑም በበኩሉ ቀላልና ከባድ የጦር መሳሪያዎችን ወደ ግዛቱ እያስገባ በመሆኑ ጉዳዩ እየከረረና እየጦዘ መምጣቱን የተመድ ሰራተኞች ስጋታቸውን እየገለፁ መሆናቸው ተጠቁሞዋል፡፡

ወያኔ ከደቡብ ሱዳን መንግስት ጋር አጥብቆ እየሰራ ከመሆኑም በላይ መስመራዊና ከፍተኛ መኮንኖቹን በምስጢር ምስራቅ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አቅራቢያ በሚገኝ ወታደራዊ መኮንኖች ማሰልጠኛ ትምህርት ቤት እያስተማራቸው ከመሆኑም ሌላ ተግባራዊ ልምምዳቸውን ደግሞ በሁርሶ ማሰልጠኛ ካምፕ አድርገው በቅርብ ግዜ መመረቃቸው ታውቆዋል፡፡

በአሁኑ ሰዓት ሁለቱ ቡድኖች እርስ በርስ እየተወነጃጀሉ አንዱ አንዱን በቃላት እየሸነቆጠ፣ ነገር እየቆሰቆሱ ወደ ከፋ ችግር ሊገቡ ይችላል ተብሎ ስጋት በመፍጠራቸው የተነሳ ወያኔ ጦሩን በምስጢር እያስታጠቀና እያዘጋጀ ይገኛል፡፡

ሀገርን እየሸጠ ያለው የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ለውንብድና ያመቸኛል ካለ እናቱንም የሚክድና ትላንት ያለውንም አላልኩም የሚል ነውናም ዛሬ ዜጎች ሁሉን የረሱ ይመስል ሀገር ወዳድ ለመምሰል ግብጽን ሲወነጅል ተደምጧል። ግብጽ ተቃዋሚዎችን እየረዳች ናት፤ ጦርነት ብትሞክረን አያዋጣትም ወዘተ ብሎ የለፈፈው የግብጹን መሪ ሆስኒ ሙባረክን አስገርሞት ይህ ሰው ምን እያለ ነው እንዲል ገፋፍቶታል። ግብጽና ወያኔ ጥሩ ግንኙነት አላቸው ሲልም ሙባረክ ገልጿል። ይህ ሀቅ ነው። መለስ በአባይ ጥያቄ የኢትዮጵያን ጥቅም አሳልፎ መስጠቱ የታወቀ ነው። የአባይ ተፋሰስ ሀገሮች ቁርጥ አቅዋም ሊወስዱ ሲነሱም መለስ ዕንቅፋት ሆኖ ቆይቷል። ግብጽ ብሔራዊ ጥቅሟን ለማስጠበቅ

ስትል የኢትዮጵያን መከፋፈልና መዳከም መፈለጓን ደብቃ አታውቅም። ከአጼው ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ ግብጽ ኢትዮጵያን እንደ ሀገር የሚበጠብጡትን ስትረዳ ቆይታለች።ከፍቶላቸዋልና ሌላ ጸረ ወያኔ ተቃዋሚን ሊረዱ ሲሮጡ አልታዩም። ስለዚህም የመለስ ጩኸት በሀገር ደረጃ ሀገር ወዳድ መባልን ፈልጎ፣ ሊያደናግር ፈልጎ መሆኑ ግልጽ ነው። መለስ ዜናዊ የኢትዮጵያን ጥቅም ያስቀድማል ብሎ ማሰብ መጠበቅ ሳይሆን ማሰብም አይገባም የሚሉ የፖለቲካ ታዛቢዎች በአባይ ጉዳይ የሀገር ጥቅም ይጠበቅ ዘንድ የመለስ ከህዲ አገዛዝ መወገዱ ወሳኝ ነው ብለዋል። ግብጽና መለስ ግን ወድዱም ጠሉም በደቡብ ሱዳንም ጥያቄ መለስተኛ ቅራኔ ውስጥ መግባታቸው የሚቀር አይደለም። መለስ ከአሜሪካ ጋር በመሆን የደቡብ ሱዳንን መገንጠል ሲደግፍ ግብጽ ግን ከአባይ ጥቅሟ የተነሳ አጋሯ ሱዳን ከዚህ ክስተት እንድትድን ትፈልጋለች።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ወያኔ የጦር ሃይሉን በተጠንቀቅ እንዲቆም ጥብቅ ትዕዛዝ ሰጥቱዋል ተብሎዋል። ለወያኔ ከፍተኛ የስጋት አቅጣጫ የሆነው ሰሜን ኢትዮጵያ በተለይ የሱዳን ድንበር አዋሳኝ የጎንደር በረሀ የሽምቅ ተዋጊዎቹ መሸሸጊያና መመሸጊያ ከመሆኑም በተጨማሪ በተለያዩ ጊዜያት ከተቃዋሚ ታጣቂ ሃይሎች ድንገተኛ ጥቃት እየደረሰበት በመሆኑ ጭምር አሁንም ስጋት ውስጥ በመውደቁ ጦሩን በተጠንቀቅ እንዲቆም ለሰሜን ዕዝ አዛዥ ትዕዛዝ ማስተላለፉ ታውቁዋል።

መለስ ዜናዊ ጦሩ በተጠንቀቅ እንዲዘጋጅ ባዘዘው መሰረት የሰሜን ዕዝ ተብሎ የሚጠራውና በወያኔው ጄኔራል በሳዓረ መኮንን የሚመራው የጦር ክፍል በሁሉም መስክ የተሙዋላ ትጥቅ እንዲዘጋጅለት እየተደረገ ይገኛል።

የሰሜን ዕዝ ተብሎ የሚጠራው የወያኔ የጦር ክፍል ሰሞኑን በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት የጦር ክፍሉ ባልደረባ የሆኑ የበታች ሹሞችም ሆኑ መኮንኖች ዓመታዊ ዕረፍት እንዳይወጡ ፣ ከካምፓቸው እርቀው እንዳይሄዱ ከመነገሩም በተጨማሪ መለስተኛ የመከለሻ ልምምድ እያደረጉ መሆኑን የደረሰን ጥቆማ ገልፆ የቀላልና የከባድ መሣሪያ ፅዳትም እየተደረገ መሆኑ ታውቆዋል።

መለስ ዜናዊ የዕዝ ጠገጉን ሳይጠብቅ በቀጥታ ለሰሜን እዝ አዛዥ ለሳዓረ መኮንን የሰጠውን ትዕዛዝ ተግባራዊ ለማድረግ ሁሉም ክፍለ-ጦሮች እየተዘጋጁ ሲሆን ከዚህ ቀደም ወደ ሱማሊያ ተልከው ጭዳ ከሆኑት ጓደኞቻቸው የተረፉት ወታደሮች አሁንም በዚህ ክፍል ውስጥ መኖራቸው ተረጋግጧል።

ከሰሜን ዕዝ በተጨማሪ በሌላው የወያኔ ጄኔራል በገዛኢ አበራ የሚመራው የመከላከያ የሎጅስቲክ መምሪያም በተሰጠው ትዕዛዝ መሰረት ትጥቅ እና ስንቆችን በተለየ አቅርቦት እያዘጋጀ ሲሆን አስቀድሞ በመምሪያው ውስጥ ለሚገኙ ከፍተኛ እና መስመራዊ መኮንኖች የአንድ ሳምንት ኮርስ እንደተሰጣቸው ታውቆዋል።